# ሐምሌ 13/1999 ዓ.ም ከእሥር ከተፈቱት

## የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራር አባላት የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

የግንቦት 97 ምርጫን ተከትሎ በአገራችን በተፈጠረው የፖለቲካ ምስቅልቅል ምክንያት የሰው ሕይወት ጠፍቶአል የብዙ ዜጎች ነጻነት ተገፎአል የድሃ ሃገር ንብረት ወድሞአል፡ በተጨማሪም በቀላሉ ሊሽር የማይችል የሥነ ልቡና ቁስል በማሕበረሰባችን ላይ ደርሷል፡፡ ይህንን አጠቃላይ ችግር በአንድ ጊዜ መፍታት ባይቻልም ቀስ በቀስ ከጊዜ ጋር እንደ ማሕበረሰብ እያገገምን ወደፊት እንሄዳለን ብለን እንደ ሃገርና ሕዝብ ማመን የወደፊት ሥራችን መሰረት ነው፡፡

የዚህ ሰፊ አገራዊ ቀውስ ሰለባዎች አንዱ እኛ የቅንጅት አመራሮች ነን፡፡ ከ20 ወራት እሥር በኋላ ሐምሌ 13/1999 ዓ.ም ከእስር ተለቀናል፡፡ ከእስር እንድንለቀቅ የተለያዩ የአገር ውስጥና የውጭ ሃይሎች ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ብዙ ኢትዮጵያዊያን በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጪ በየሃይማኖት ቤታቸው ጸሎት አካሂደዋል፡፡ሌሎችም ከእኛ ጋር ያላቸውን አጋርነት ለፀሃይ ግለትና ለብርድ ሳይበገሩ በተለያየ ቦታ በሕዝባዊ ሰልፎች ገልፀዋል፡፡ ለረጂም ቀናት በፆም ምህላ አድርገዋል፡፡ የሃገር ሽማግሌዎች ችግሩን በሰላምና በእርቅ ለመፍታት ላይ ታች ብለዋል፡፡ በቅድሚያ ለእነኚህ ሁሉ ዜጎቻችን፡ እንዲሁም ኢትጵያውያን ላልሆኑ የመብት ተከራካሪዎችና የዴሞክራሲ ጠበቆች በአደረጉት ጥረት በእስር እያለን ይሰጡን የነበረውን የሕሊና እረፍት በማስታወስ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ሕይወታቸውን ላጡት ዜጎቻችን ያለንን ከፍተኛ አክብሮት የምንገልጸው እኛም ሆንን ሌሎች ኢትዮጵያዊያን መቼም የማንረሳቸው የዴሞክራሲ ሰማእታት መሆናቸውን በማስታወስ ነው፡፡ለቤተሰቦቻቸውም ፈጣሪ መጽናናትን እንዲሰጣቸው ሁሌም በጸሎታችን አንዘነጋቸውም፡፡

እኛን ከእስር ለማስፈታትም ሆነ በፀብና በእልህ አጣብቂኝ ውስጥ የገባውን የኢትዮጵያን ሰላማዊ የፖለቲካ ሂደት ከገባበት ለማውጣት የተወሰኑ የሃገር ሽማግሌዎች ቢያንስ ላለፉው አንድ ዓመት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የጥረቱ መሠረታዊ መንፈስ እኛን ከእስር ማስፈታት ብቻ ሳይሆን ሀዲዱን የለቀቀውን የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ጉዞ ወደ ተገቢው መስመርና አቅጣጫ መመለስ ነው፡፡

ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ሽማግሌዎቹ አስፈላጊ ነው ብለው ያመኑበትንና እኛም ከልባችን የተቀበልነውን የአገራችን ባሕል በሆነው ይቅርታ መባባል መንፈስ ችግሩን ለመፍታት ተስማምተናል፡፡

ያለፈውን በሚመለከት ጥፋት ያጠፉትን ሃይሎች ሁሉ ይቅር በማለት፡በዚህ ሂደት የተጎዱትን ከጉዳታቸው የሚያገግሙበትን መንገድ በመሻት በዋነኛነት ደግሞ የወደፊቱን በመመልከት ከእርቁ በኋላ በሚፈጠረው አጠቃላይ ሁኔታ ላይ በማተኮር፡ ሁኔታዎች ከሁከቱ በፊት ወደነበሩበት መመለስ አስፈላጊ መሆኑን ተማምነናል፡፡

ጥረቱም በይበልጥ በዚህ ሁኔታና ከዚያም በኋላ በተፈጠረው የተበከለ መንፈስ ምክንያት ሁላችንም የምንወዳት ሃገራችን የበለጠና በኋላ ልትወጣ ከማትችልበት ማጥ ውስጥ እንዳትገባ

ለመከላከል ያለመ ነው::ከጅምሩም እኛ የቅንጅት አመራሮች በተቻለን መጠን በጥላቻ ባለመመራትና ተጎዳን የምንለውን ሁሉ በትእግስት በመያዝ እስከመጨረሻው ተጉዘናል::

ዘላቂ የሆነ የእርቅ መንፈስን ለማስፈን አስፈላጊ ናቸው በተባሉ የተለያዩ ነጥቦች ላይ ከሽማግሌዎች ጋር ሰፊ ውይይቶችን አድርገናል::በብዙ ነጥቦችም ላይ ተስማምተናል:: የደረስንባቸው ስምምነቶችም የእኛና የሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ ጉዳዩ በሚመለከተው ሌላው አካል ዘንድም ስምምነት እንደተደረሰባቸው በሽማግሌዎች ተገልጾልናል::ምንም እንኳን በመጨረሻው በመንግሥት በኩል ስምምነት ተብሎ የተገለጸው ከዚህ ከሽማግሌዎች ጋር ከተደረሰው ስምምነት የተለየ ቢሆንም የስምምነቱን እውነተኛ ይዘት ወደፊት እነኚሁ የሃገር ሽማግሌዎች አስፈላጊ በሆነ ጊዜና በሚመቻቸው ሁኔታ ለሕዝቡ ይገልጹታል ብለን እናምናለን:: ስምምነቱ ከተፈጸመም በኋላ በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በሰፊው እየተሰጠ ያለውን የፕሮፓጋንዳ ምንነት የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅጡ እንደሚያውቀው በውል እንረዳለን:: በዚህም ፕሮፓጋንዳ ምክንያት ቅንጅት በሕዝቡ ዘንድ ያለው ተሰሚነት ቅንጣት ታህል እንኳዋን ዝቅ ይላል ብለን አንገምትም::ይህንንም ከተፈታን በኋላ ሕዝቡ ያሳየን አክብሮትና የሰጠን አስደናቂ ፍቅር አረጋግጦልናል::

ስለዚህም ለተሰነዘረው ፕሮፓጋንዳ አጸፋ መልስ መስጠቱ ሽማግሌዎችም ሆኑ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲፈጠር የፈለጉትንና እኛም ያመንበትን መንፈስ የበለጠ ከመበከል ውጪ ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑን ተገንዝበን አልፈነዋል::

ይልቁንም እኛ እንደ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ባለፈው ላይ ከማተኮር ወደፊት ማየትን መርጠናል::ይህም የኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ድርጅታችን የተመሰረተበትንና የታገለለትን የኢትዮጵያ ሕዝብም ከልቡ የሚፈልገውንና የሚገባውን ዴሞክራሲያዊ ስርአት በእግሩ ለማቆም የሚደረግ ትግል ነው::እኛ የቅንጅት አመራሮች ለዚህ ትግል ያለንን የማይነቃነቅ ቁርጠኝነት እናረጋግጣለን::የዚህ ሂደት የመጀመርያው እርምጃ በስምምነታችን መሰረትና የሃገር ሽማግሌዎች ለማስፈጸም ቃል ከገቧቸው ጉዳዮች አንዱና ለአሁኑ ጊዜ ዋና የሆነው ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ በእስር የሚገኙት በሙሉ ከእስር ተፈትተው ማየት የእኛም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ አጀንዳ ስለሆነ ይህንን ጉዳይ የሃገር ሽማግሌዎች በአስቸኳይ እንዲያስፈጽሙ እናሳስባለን:: ይህ ከመሆኑ በፊት ግን በሌሎች አጀንዳዎች ላይ ወደፊት መሄድ አስቸጋሪ መሆኑን እንገነዘባለን::

በመጨረሻም እኛ የቅንጅት አመራሮች ኢትዮጵያችን አሁን ከገባችበት የፖለቲካ አጣብቂኝ ወጥታ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲፈጠር የጀመርነውን ትግል እንደምንቀጥል: ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሃገራችን መፈጠር:እኛ ከያዝነው አቋም ጋር ከሚስማሙ ከማናቸውም ሃገራዊ ሃይሎች ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን::በቀጣይነትም ቅንጅቱ አሁን በሀገራችን ባለው ሁኔታ ላይ በሰፊው መክሮ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለሕዝቡ ይገልጻል::

| | |
|---|---|
| ወ/ሪት፡ ብርቱካን፡ ሚደቅሳ | ዶ/ር፡ ኃይሉ፡ አርአያ |
| ተ/ም/ ሊቀመንበር | የድርጅቱ፡ ቃል አቀባይ |
| 18/11/99 ዓ.ም | 18/11/99 ዓ.ም |